# ፍርድን ለራስ ምርትን ለአግማስ

እንደ መንደርደሪያ፡

ድሮ ድሮ ነው።አንድ አዛውንትና ባለቤታቸው ሁሉንም ልጆቻቸውን ድረው ኩለው የመጨረሻዋን ሴት ልጃቸውን ላቅመ_ሄዋን እስክትደርስ ጊዜውን ይጠብቁ ነበር። ጊዜም ሯጭ ነውና ኮረዳዋም ለተጠበቀው ጋብቻ ደረሰች። አማጭዎችም ወደ ወላጆቿ ቤት መጉረፍ ጀመሩ። ሁኔታውን የተመለከተችው ኮረዳም አጋጣሚውን በመጠቀም ከዕለታት አንድ ቀን ማግባት የምትፈልገው ቀለኛ እንጅ ደገኛ አለመሆኑን ለናቷ ሹክ አለቻቸው። እናትም የልጃቸውን ፍላጎት ለማሟላት ሲሉ የሚመጣውን የደገኛ አማጭ በሙሉ ፊት እየነሱ መለሱት። አባት ግን በባለቤታቸው ሁኔታ ግራ ተጋብተው ነበር ; ሁኔታውን ግልፅ ለማድረግ ምን አስበሻል? ሲሉ ጠየቁና ተወያይተው የልጃቸውን ፍላጎት ለማሟላት ትስማሙ። አባትም ከዚያች ዕለት ጀምሮ እንደ ቀልድም እንደ ቁምነገርም እያደረጉ ልጃቸውን ለቀለኛ እንጅ ለደገኛ እንደማይድሯት ዜናውን አሰራጩ።

ከዚህ በሁዋላ ከደጋ ሳይሆን ከወደ ቆላ የሚመጡ አማጭዎች ተበራከቱ። በሁኔታው መለወጥ እናት የተደሰቱትን የክል ግን አባት አልተደሰቱም ነበር።በርሳቸው እምነት የቀለኛ ወንድ ሚስቱ ጠመንጃው ነው። የቆላ ወንድ ውሎው ዱር። አዳሩ ዱር። ልጄን ያስርባታል የሚል ስጋት ነበራቸው ። በመጨረሻ ግን ባለቤታቸውን ላለማስቀየም ሲሉ ለሚመስላቸው ላንደኛው ቀለኛ አማጭ እሽታቸውን ሰጡና ሰርገው ልጃቸውን ዳሩ።

ሙሽሮችም ጊዜአቸውን ጠብቀው ለሶስት ጉልቻ በቁና ራሳቸውን ችለው ጎጆ ወጡ። በጋውንም አልፈው ወደ በልግ ተሸጋገሩ። ክረምቱም ግም ግም ማለት ሲጀምር መሬቱን ጦም ላለማሰደር ሲሉ ያላቸውን አሟጥጠው ዘሩ።ከዚህ በሁዋላ ግን ባልም በዋለበት ማምሸትና ማደር አዘወተረ። ሚስትም ባዶ ጎጆ ታቀፎ ማደርን እየተለማመደችው መጣች። ያባት ትንቢትና ፍራቻም እውነቱ በሙሽራዋ ልጃቸው ህሊና ስፍራ እያገኘ ሄደ። በዚህ መሃከል ውሃው ሳይሞላ የወጥ ጨውና ቅመማቅመም ለመሸመት ወደ ዳባት ለገበያ በሚሄዱት ጎረቤቶቿ ለወላጆቿ መልዕክት አስይዛ ሰደደች። መልዕክቷም አንዲት ዘለላ ሃረግ ነበረች። ሽንብራ ያበቅላል ወገራን ላረሰው፤ የምትል። አባትም መልዕክቱ ሲደርሳቸው አዘኑ። የፈሩትም መድረሱን ለባለቤታቸው ለወ/ሮ ማንችሎ ነገሯቸው። ወላጆች ገበያተኞቹ ሲመለሱም ለልጃቸው የሚችሉትን ሁሉ ካስቋጠሩ በሁዋላ አባትየውም ለልጃቸው የመለሱት በዘለላ ሀረግ ነበር። እንዲህ ብለው፡

የሚበላ አይጠፋም ለጠረጠረ ሰው።<br>
ወገራ ብዙ ዘር የሚያፈራ አገር ነው።

ወገራ ልጅቷ እንዳለችው ላረሰው ሰው ብዙ ሽንብራ ያበቅላል።ኢህአፓም እንደ ወገራ ላረሰው የማያበቅለው ነገር የለም። ብርሀነ መስቀልን፤ ጌታቸው ማሩን፤ አራርሶን፤ብርሃኑ ነጋንን፤አንዳርጋቸው ፀጌን፤ ክፍሉ ታደሰን፤ዛሬ ደግሞ መርሻንና; ጌታቸው በጋሻውን አብቅሏል።

በኢህአፓ ውስጥ የሚበላ ስለማይጠፋ ለጠረጠረ ሰው ብዙ ብዙ ገና ብዙ ሽንብራ ይበቅላል። ስንቶቻችን ሽንብራ ጠርጥረን እንደምናውቅ ዕርግጠኛ አይደለሁም።ያልጠረጠርን መኖራችን ግን አይካድም። ኢህአፓ ዕምነት ነው። ዕምነት ደግሞ ማተብ ነው። ፍፁም ነው ዕምነቴ የትግሎ ነው ህይወቴ እንዲሉ። ግና ግና ዕምነት ክህደትን ሲወልድ አዋላጅ ሆነን እስከ መቸ እንደምንኖር አልገባህ እያለ ተቸግሬአለሁ።

አቶ መርሻ ዮሴፍ ወያኔን ይቅርታ ጠይቀን እንግባ ሲሉ ዕምነት ክህደት የፀነሰ መሆኑን መጠርጠር ተስኖን ይልቁንም ተልዕኮአቸውን እንዲፈፅሙ የድሮ ጓዶችን እንዲያሰባስቡ ሃላፊነት ሰጠናቸው። በራሳችን ገንዘብና መዋቅርም በድርጅታችን ውስጥ የራሳቸውን አንጃ እንዲመሰርቱ አመቻችተን ቀረብንላቸው።

አብራሃም በየነ -------------------ይቀጥላል